ዝንቱ ውእቱ ትእምርተ ሰላም፤

ዘረሰዮሙ አሐደ ለክልኤሆሙ ፤ ኤፌ ም ፪ ቁ ፲፬

፲፰ኛ ዓመት ቁጥር ፲

አ፡ አ፡ ጥር ፰ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ. ም.

# ተክለ፡ሃይማኖት ።

ይህ ድርሰት ለሃይማኖትና ለምግባር ለጊዜውም ዜና መዋዕል መግለጫ የንባቡን ቀጥተኛ ትርጓሜ ከመከተል ጋር ስለ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ መታሰቢያ
ተክለ ሃይማኖት ተብሎ ተሰየመ ።

| | | |
|---|---|---|
| የድርሰቱ ዋጋ ባገር ውስጥ ባመት ብር 1.20<br>» » አንዱ 0.5<br>ለውጭ አገር እጥፍ ይሆናል ። | በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የታሪክና ዜና ማደራጃ<br>ጽሕፈት ቤት ኃላፊነት ታተመ ። | በወር ሁለት ጊዜ ይወጣል ።<br>የስልክ ቁጥር 13090/4<br>የፖስታ ሳጥን ቁጥር 12.83 |

## በእምነትና በጥምቀት

### የሚገኘው ልጅነት ።

ጥምቀት ከሰማያዊው ንጉሥ ያልተ ወለደውን ሰው እንዲወለድና ከመንግ ሥቱም ተካፋይ ሆኖ የመንፈስ ፍሬ የሆኑትን ደስታን ሰላምን ፤ ትዕግሥትን ፤ ቸርነትን ፤ በጐነትን እምነትን፤ የዋህነትን፡ ራስን መግዛትን ተጐናጽፎ ዓለም ሳይ ፈጠር የተዘጋጀለትን መንግሥት ይወር ሳል ገላትያ ፭. ፳፪. ይኸውም ቃል



ጌታችን ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ ።

የተጠመቀ ይድናል ያልተጠመቀ ግን ይፈረድበታል በሚለው በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መንግሥተ ሰማያትን የሚ ወርስ አማኝ ብቻ ነው ። ማርቆስ ፲፮ -፲፮ በኃጢአት የአረጀው ሰውነታች ንም በጥምቀት በአገኘው ልጅነት ይታ ደሳል ፤ ይኸውም ሲባል ሰው ከተወ ለደ በኋላ እንዴት አድርጎ ሁለተኛ ለመወለድ ይችላል የሚል ጥያቄ በል ቡናችን ይደቀን ይሆናል ።

እውነት ነው ይህን የመሰለ ረቂቅ ምሥጢር ከባድ መሆኑ አይዘነጋም ሆኖም ጌታ ለኒቆዲሞስ የሰጠው መልስ በቂ መረጃ ሊሆነን ስለሚችል ከዚህ ላይ ማስታወስ ይጠቅመናል ። መልሱም እንዲህ የሚል ነው ፤ እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያ ይ አይችልም ፤ ብሎ ጌታ ለኒቆዲሞስ ቢነግረው ነገሩ በጣም አስቸጋሪ ስለሆነ በት እሱም በበኩሉ ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት አድርጎ ሊወለድ ይች ላል ? ሁለተኛስ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን ? ብሎ ቢጠ ይቀው ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰ እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግ ዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይች ልም ፤ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመ ንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው ፤ ስለ ዚህ ዳግመኛ መወለድ ያስፈልጋችኋል ይህን ስለአልሁህ አታድንቅ ነፋስ ወደ ሚወደው ይነፍሳል ድምፁንም ትሰማ ለህ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴ ትም እንደሚሔድ አታውቅም ። ከመንፈ ስም የሚወለደው ሁሉ እንዲሁ ነው ብሎ በምሳሌ አስረድቷል ዮሐንስ ፫. ፱.

ከቡራን ምእመናን፤ ሁልጊዜም ቢሆን የእግዚአብሔር ፀጋውና መንፈሱ ሲያ ድርብን የእግሩ ኮቴ የመልኩ ሁኔታ ረጅም ይሁን ወይም አጭር ፤ ቀይ ይሁን ወይም ጥቁር ሊታወቅንና እን ዲህ ያለ ነው ለማለት አንችልም ።

www.ethiopianorthodox.org

ምክንያቱም በጣም ረቂቅ ስለሆነ ሲያድርብን የምናውቀው ሃይማኖትን ስናጸና ፤ ምግባር ፤ ትሩፋት ስንሠራ ፤ ለክርስቶስ ስንመሰክር ብቻ ነው ። ይኸውም ለክርስቲያን ሁሉ ጽኑ እምነት የሚባለው መሣሪያ ሁል ጊዜ እንዳይለየን ያስጠነቅቀናል ማርቆስ ፲፫. ፲፮.

እምነት ከሌለን እንኳን የማይታየውን የእግዚአብሔር መንፈስ ማየት ይቅርና የሠጠውን ወርቅና ብር በምስክር ፊት ፈርሞ የተቀበለውን ለጊዜው የሚያመልጥ እየመሰለው አንድ አንዱ እምነትን ይለውጣል።እንዲህ ያለው ተግባር ግን እንኳን በክርስቲያን ዘንድ ይቅርና በአረማውያንም ቢሆን ሕገ ወጥ ተግባር መሆኑን ስለምናውቅ በክርስቶስ ስም አምነን ለተጠመቅን ምእመናንእኛ ሳናያቸው በላያችን አድረው የሚያጽናኑን ብዙ የእግዚአብሔር ስጦታዎች አሉ ለዚህም ደጋፊ የሚሆን ከዚህ በላይ ከጠቀስኳቸው ምዕራፎች ሌላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሰፊው ያስረዳናል ። የአባቶቻችንም ተረት እንዲህ ይላል።የአቡነ ዘበሰማያት ጦር ሲወጋ እንጂ ሲወረወር አይታይም እየተባለ የሚነገረውን ማንኛውም ክርስቲያን አንድ አንድ ችግር ባጋጠመው ጊዜ የክርስቲያኖች መጠጊያ ወደሆነችው ቅዕረ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብቶ የችግራችን መወያያዎች የሆኑ የጸሎት መጻሕፍትን አንግቶ በውነት የሚሠራና የተሰለፈ ክርስቲያን ሁሉ ሲያሸንፍእንጂ ሲሸሽ አይታይም ። ክቡራን ምእመናን ።

በእምነትና በጥምቀት የሚገኘው የእግዚአብሔር ልጅነት ረቂቅ ወይም ጥልቅ ምሥጢር ስለሆነ እስከ ሚቻለን ድረስ መርምረን ለማወቅና ለመረዳት መሞከር ነው ። የሚቻለውን ምሥጢር ደግሞ ጥርጥር በሌለው እምነት ይሁን ብለን እንድንቀበለውና የበረከቱ ተሳታፊ እንሆን ዘንድ ለቸርነቱ ውሳኔ የሌለው አምላክ ሁል ጊዜ አይለየን ። አሜን ።

ሞገስ ኪዳነ ማርያም ።

# የ ቃ ና ሠ ር ግ ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የገሊላ አውራጃ በምትሆን በቃና የአደረጋት የተአምራቱ መጀመሪያ ይህችናት ። ክብሩንም በዚችው ዕለት ገለጸው ደቀ መዛሙርቱም አመኑበት ።

ክርስቶስ በገዳም ፵ መዓልት ፵ ሌሊት በጾም ፤ በጸሎት ተወስኖ ከሰነበተ በኋላ ፵ው ቀን ሲፈጸም እናቱ ድንግል ማርያም ከአለችበት ቦታ በገሊላ ተገለጸ ወዲያው በሦስተኛው ቀን የገሊላ አውራጃ በምትሆን በቃና የአንድ ሀብታም ልጅ ሠርግ ስለነበር እናቱንና ደቀ መዛሙርቱን ይዞ እንዲመጣ ከፍ ባለ ክብር ተጠራ ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ጥሪውን በክብር ተቀብሎ ከእናቱ ድንግል ማርያም ጋር ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ ወደ ሠርጉ ቤት ሄደ ፤ ያም የሠርጉ ባለቤት እጅ ነሥቶ አክብሮ ተቀብሎታል ። ክርስቶስም የዚህን ሰው ትሕትናና ቅንነት እንዲሁም ተአማኝነቱን ተመለከተ ።

ይህ ሰው በሀገሩ የታወቀና የተከበረ ከፍ ያለ ሰለ ነበር የሠርጉ ድግስ በመጠኑ ቢሆንም እንኳ አንዱን ጠርቼ አንዱን ወይም ሌላውን እንዳልምን እተዋለሁ ብሎ በዚች ሀገር የሚገኙትን ባላባቶችና ሽማግሎችንም በብዛት ጠርቶ ስለነበር የሚጠጣው የወይን ጠጅ ስለ አለቀበት ብዙ ሰው ጠርቻለሁ ከቶ ምን ይበጀኝ ይሆን ? እያለ ከቤተ ሰቡ ጋር ሲነጋገር የኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ድንግል ማርያም ሰምታ ልጇዋ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ልዩ ልዩ ተአምራት ማድረጉን ታውቃለችና ልጄ ሆይ እኒህ ሰዎች የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው እሱም መልሶ ጊዜዬ ገና ነው አልደረሰም አላት ። እናቱም ይህን የልጇዋን ቃል ሰምታ አገልጋዮቹን የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው በዚያም እንደ አይሁድ ልማድ የሚያንፁባቸው የድንጊያ ጋኖች ነበሩ እነላቸውም እየአንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ሦስት ሦስት እንስራ የሚይዙ ናቸው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የዚህን ሰው ችግርና ጭንቀት ተመልክቶ የናቱን ቃል ሰምቶ ልመናዋንም ተቀበለ ። ተአምራቱም እንዲገለጽና በዚሁ ዕለት የተአምራቱ መጀመሪያ እንዲሆን ይህን ዕለት መረጠ ። ከዚህ በኋላ መድኃኒታችን ጋኖቹን እስከ አፋቸው ሙሏቸው ብሎ የሠርግ ቤቱን ሠራተኞች አዘዘ እነሱም እንደ አዘዛቸው አደረጉ ። ወዲያው በአምላካዊ ቃሉ በተናገረ ጊዜ ጥሩው ውኃ ወደ ወይን ተለወጠ ለአስተዳዳሪው (ለምርፋቁ አለቃ) ቀድታችሁ ስጡት አላቸው እነሱም እንደ አላቸው ለምርፋቁ አለቃ ከጋኑ በጥቂቱ ፈሰቅ አድርገው ወስደው ለሠርጉ አለቃ ሰጡት።የምርፋቁም አለቃ ይህን የወይን ጠጅ የሆነውን ውኃ በቀመሰ ጊዜ አደነቀ ። ከወዴትም እንደመጣ አላወቀም ነበር ። ነገር ግን ውኃ የመሉት ሠራተኞች ያውቁ ነበሩ ።

የምርፋቁም አለቃ ወዲያው ሙሽራውን አስጠርቶ ወዳጄ ምነው መልካሙን የወይን ጠጅ ወደኋላ አደረግኸው ? ብሎ ቢጠይቀው ሙሽራው የተደረገውን ተአምራት ያውቅ ነበርና የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስን ለዚሁ በዓል ተከፋይ ሁኖ ሠርጉንም እንዲባርክልኝ ጠርቼው ነበርና የእሱ በረከትና የእሱ ምርቃት ይህን ጥሩውን ውኃ የወይን ጠጅ አደረገው አለው ። ወዲያው ሙሽራውና የምርፋቁ አለቃ በዚሁ ሠርግ ቤትም ተሰብስቦ የነበረው ሕዝብ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክ መሆኑን አምነው ይህን ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠውን ውኃ ጠጥተው ተለያይተዋል ። ይህም ዕለት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከሁን ድረስ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያው ተአምር የተፈጸመበት ዕለት ነው እያለች ቤተ ክርስቲያናችን ታስተምራለች ። ይህ በዓል ከጌታ በዓላት ፩ዱ ነው ። በዚህ ዕለት የኢትዮጵያም ምእመናን ቤተ ክርስቲያንን እጅ በመንሳት በዓሉንም በማክበር ከፍ ባለ ክብር ያከብሩታል ። የቃና ዕለት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሴቱ በዕልልታ ፤ ወንዱም በሆታ ፤ ክህናቱም በማኅሌትናበዝማሬ ሲያመሰግኑ ይውላሉ ሕፃናቱም በዘፈን በሌላም ልዩ ልዩ በሆኑ ጨዋታዎች ሲጫወቱ ለተመልካችም ሆነ ለተጫዋች በጣም ያስደስታሉ ። አሁንም ይህን የጌታን በዓል በዛሬው ዕለት አክብረን እንድንውል በዓሉንም የተባረከ እንዲያደርግልን እግዚአብሔር ይርዳን ። መ. መልአኩ ፈለቀ።

# የ ወ ን ጌ ል

## ሆስፒታል በነፃ ያክማል ።

አባታችን አዳም ከፈጣሪው ትእዛዝ በመተላለፍ ከሥላሴ የጸጋ ልደት ያገኘውን ልጅነቱን አስወስዶ ፃዕርነገዳር ከሴ ለባት ከመልከሟ ቤቱ ከገነት መውጣቱን ሁላችንም እናውቃለን ።

የሁሉ መገኛ የሆነው እግዚአብሔር ግን ምሕረት፥ ቸርነት የባሕርዩ በመሆኑ መጽሐፈ ኩፋሌ እንደሚነግረን በ፰ ቀን ተኩል (፳፻ ፳፱ ዘመን) ከልጅ ልጅህ ተወልጄ እስከ አድንኅ ድረስ ጥረህ፣ግረህ ብላ በኋላ ግን ወደ ጥንት ቦታህ እመልስሃለሁ ብሎ የታመነ ተስፋ ሰጠው እንጂ እንዲያው ከገነት አስወጥቶ አልጣለውም ።

www.ethiopianorthodox.org

ይኸውም ዘመን ሲፈጸም ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም
ተወልዶ ለዘመዶቹ እየታዘዘ ማለት ከኃ
ጢአት በቀር የሰውን ሥራ እየሠራ ቀስ
በቀስ ከአደገ በኋላ በ፴ ዘመኑ ያን አባ
ታችን አዳም በፈቃዱ ያስወሰደውን
ልጅነት ለመመለስ የአዳምም የዕዳ ደብ
ዳቤ በዚያው ተቀምጦ ስለነበር ለመደ
ምሰስ ፤ የዮርዳኖስንም ውኃ ለመቀደስ
ሲል ሰማያዊው አምላክ በምድራዊው
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ።

መጠመቁም ንጹሕ ርሱን ተዋሕዶን
ለመኖር የንጽሕና አድነትን ይሰጠን ዘንድ
ነው እንጂ በርሱ በባህርዩ ጉድለት ኑሮ
በት ፤ ሊጠቀምበት የተጠመቀ አይደለም
ንጹሕ ርሱን ተዋሕዶ ለመኖር የሚያበ
ቃው ዋናው መሠረቱ ጌታችን ራሱ
«ወትእዛዛተ ጽድቅ በወንጌል መጠወ»
ለጽድቅ የሚያበቃውን ትእዛዝ በወንጌል
ሰጠ እንደሚለው ሁሉ በድንቁርና ደዌ
የተያዙ የዚህ ዓለም ሕዝቦች በነፃ ይታ
ከሙበት ዘንድ መልክዓን ሆስፒታል
ወንጌልን ሠርቶልናል ።

ከዚህ ላይ ወንጌልን በሆስፒታል
ከመሰልን ዘንድ ልዩ ልዩ ድርጅቶች
ስለ አሏት በጥቂቱ መግለጽ ይኖር
ብናል ለዚችም ሆስፒታል ፯ ሮቶች
(ምሥጢራት) አሏት እነዚህም ፤ ጥም
ቀት—ሜሮን—ቊርባን—ንሥሐ—ቀንዲ
ል—ክህነት—ተክሊል ናቸው ከነዚህም
ጥምቀት ሜሮን ክህነት ሦስቱ አይደገ
ሙም የቀሩት ግን የሚደጋገሙ ናቸው
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሆስ
ፒታልን ሲመሠርት ዶክተሩ ራሱ ሲሆን
ለጊዜው ሠራተኞች የነበሩት ፲፪ የጤና
መኰንኖች (ሐዋርያት) ፸፪ ድሬሰሮች
(አርድዕት) ፴፮ ነርሶች (ቅዱሳት አንስት)
በጠቅላላው መቶ ሐያ ቤተ ሰቦች ናቸው።

እንዲሁም ለሰው ልጅ ሁሉ ሙሉ
ጤንነትን የሚሰጡ መድኃኒቶች ሥጋ
ውና ደሙን ፤ ጾምና ጸሎትን ፤ ፍቅርና
ትሕትናን እነዚህን የመሳሰሉትን ነገሮች
አዘጋጅቶ በዲያብሎስ ምቀኝነት ምክን
ያት በኃጢአት በሽታ ተይዞ አምስት
ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲጨነቅና
ሲሰቃይ የኖረውን ይህን ዓለም ድውይ
እየፈወሰ ሙት እያስነሣ ፤ ለምጽ እያነፃ ፤
ዕውር እያበራ ፤ አንካሳ እያረታ «እናንት
ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደኔ
ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ ቀንበሬን በላያ
ችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ
በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳችሁም ዕረ
ፍት ታገኛላችሁ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም
ቀሊል ነው ና ይላቸው ነበር ማቴ ፲፩
፳፰—፴ ።

እንዲህም አድርጎ የዘለዓለም ሕይወት
የሚገኝባትን ወንጌልን ሦስት ዓመት
ከሦስት ወር አስተምሮ ወደ ሰማይ በሚ
ያርግበት ጊዜ በአባቴ ቤት ብዙ መኖ
ሪያ አለ ሲል የሰው ልጅ ሁሉ በጥ
ምቀት በር ከገባ በኋላ በልዩ ልዩ ሥራው
የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ መሆኑን አረ
ጋግጦልናል ። ዮሐንስ ፲፬ ፪ ።

በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶ
ዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንም ሰውን ሁሉ
የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ለማድረግና
ይልቁንም እኔ በሄድኩበት መንገድ ተከ
ተሉኝ ያለውን አምላካዊ ቃል በደንብ
ስለምታውቀው የወንጌል መልክተኞቿን
በሀገሯም ሆነ በውጭ አገር በብዛት
እየላከች ከጥምቀት በአፍአ ያሉትን
ሕዝቦች በእየደጃፋቸው እየሄዶች በወ
ንጌል ሆስፒታል ትምህርቷ በነፃ ታክ
ማቸዋለች ።

እግዚአብሔር በነቢዩ አድሮ "በት
እዛዜም ይሄዱ ዘንድ ፍርዴንም ይጠብ
ቁና ያደርጉ ዘንድ አንድ ልብ እሰጣቸ
ዋለሁ በውስጣቸውም አዲስ መንፈስ
እሰጣለሁ ከሥጋቸውም ውስጥ የድንጋ
ይን ልብ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ
እሰጣቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑ
ኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ" ያለው
ትንቢት በበለጠ የተፈጸመው ዛሬ በያ
ዝነው ጊዜ መሆኑ ግልጽ ነው ። ሕዝ
፲፩ ፣ ፲፱-፳፩ ።

አንባብያን ሆይ ።

በኢትዮጵያ ግዛቶች ውስጥ የአዲ
ሶች አማንያን ቊጥር በየጊዜው እየበረ
ከተ ስለሄደ እግዚአብሔር በሰዎች አድሮ
የሚያደርገውን ታምራት በማድነቅ ታመ
ሰግኑት ዘንድ መንፈሳዊ ልመናዬን አቀ
ርብላችኋለሁ ።

የጃሬ አውራጃ ግዛት
የወንጌል መልእክተኛ ጎሩይ ለገሠ ።

# ልዩ ልዩ መንፈሳውያን
## ዜ ና ዎ ች ።

፩ኛ· ከአርጡማ በጃሬ አውራጃ
ለስብከተ ወንጌል የተላኩት መ. ጎሩይ
ለገሠ ከሄዱበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ አረ
ማውያንንና እስላምን እንዳጠመቁ ከሁን
በፊት ደጋግመን በጋዜጣችን ገልጠናል።
አሁንም ትጋታቸውን በመቀጠል ከአለ
ፈው ከመጋቢት ወር ፶፰ ዓ. ም. እስከ
ኅዳር ወር ፶፱ ዓ ም ፲፬ ሰዎች አጥም
ቀው ለቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ
ክርስቲያናችን አዲሶች አባሎች አስገ
ኝተዋል ። በዚህም ሥራቸው ዜና ቤተ
ክርስቲያን ጋዜጣችን ምስጋናውን ያቀ
ርባል ።

፪ተኛ. ከደምቢዶሎ (ሀ) በወለጋ
ጠ. ግዛት በቄለም አውራጃ በስዮ ወረዳ
ጠ. ግዛት ሐዋ
በሐዋኒ ማሎኒ ም. ወረዳ ግዛት ሐዋ
ቅዱስ ሚካኤል የተባለው ደብር ኅዳር
፲፪ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ ም የሚካኤል ክብረ
በዓል ተከብሮ ውሎ በ፲፫ኛው ለቅዳሚ
አጥቢያ ባልታወቀ ምክንያት ከቤተ
መቅደሱ እሳት ተነሥቶ የጉልላቱን ቆር
ቆሮ አቃጥሎ ሌላውን አንዳች ነገር
ሳያደርግ በሕዝበ ክርስቲያኑ ብርታት
ጠፍቶአል።በንዋየ ቅድሳቱም ላይ አንድ
ም ጉዳት አልደረሰም ።

(ለ) በዚሁ ወረዳ በደምቢዶሎ
ከተማ አካባቢ የሚገኙት ሕዝበ ክርስቲ
ያን ማንም ሰው ሳያስገድዳቸው መንፈ
ሳዊ ኃይል አነሳስቶአቸው እሑድ እሑድ
የስብከተ ወንጌል መስሚያ ቦታ ስለ
አልነበረ ሀብት ያላቸው በሀብታቸው፤
የመሐንዲስነት ችሎታ ያላቸው በጉል
በታቸው ከ፷፻ ብር በላይ የተገመተ
ከግንብ የተሠራ ክዳኑ ቆርቆሮ የሆነ
ደንበኛ የስብከት አዳራሽ ሠርተዋል ።

ይህም አዳራሽ በብፁዕ አቡነ ዮሴፍ
ተባርኮና ተመርቆ ከጥቅምት ፳፯ ቀን
መድኃኔ ዓለም ከሚከበርበት ዕለት
ጀምሮ ሥራውን ቀጥለዋል ሲሉ የክ
ፍሉ ሰባኬ ወንጌል አቶ ዕዝራ መኰ
ንን ገልጸውልናል ።

፫ተኛ. ከ ጎ ባ በባሌ ጠ. ግዛት
ጎባ ከተማ የሚገኘው የቅድስት
ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቅጽሩ ፈርሶ
ስለነበር በዚሁ ቤተ ክርስቲያን በሁለት
ክፍል የሰንበተ ሰንበታት ሰንበቴ የሚ
ጠጡት ምእመናን በመተባበር ፩፻ ብር
አዋጥተው በሻምበል ከበደ መኰሪያና
በአቶ መልሴ ደስታ አተጋጊነት ከመ
ስከረም ወር ፶፯ ዓ. ም. እስከ ታሕሣሥ
ወር ድረስ ተሠርቶ ተፈጽሟል ሲሉ
የክፍሉ ሰባኬ ወንጌል መ| ተውህበ
ምሕረት ገልጠውልናል ። ይህን የመ
ሰለውን መንፈሳዊ ሥራ የሚፈጽሙ
ትን ደጋጎች ምእመናን በሰፊው እናመ
ሰግናቸዋለን ።

www.ethiopianorthodox.org

# ምስጋና

የባሌ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ክቡር ፊታውራሪ ወርቁ እንቁሥላሴ የዚህ ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ለሀገረ ስብከቱ ጽ/ ቤትና እንዲሁም ለየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚያደርጉት ርዳታ ከፍ ያለ በመሆኑ ምእመናኑ በመደሰት ላይ ናቸው ፤ በዚሁ መንፈሳዊ ቅስቃሴ ሕዝቡ በበጎ ፈቃዱ ገንዘብ እያዋጣ ብዙ ቤተ መቅደሶችንና የስብከት አዳራሾችን ለማነጽ ችሏል ፤ ይህም መልካም አርዓያ የክቡር እንደራሴው መንፈሳዊነት በመሆኑ ሕዝቡን ሁሉ በመንፈስ ስለቀሰቀሰው ሁሉም ወደ ሕይወት መንገድ ሲጓዝ ይታያል በማለት ከሀገረ ስብከቱ ከፍ ያለ ምስጋና ቀርቦላቸዋል ። ስለዚህ ከድምፅ ሥራ ይጮሃል እንደተባለው እንደዚህ ያለ ክርስቲያናዊ ሥራ መሥራት ሌላ ውንም ሕዝብ ወደ መንፈሳዊነት ከመምራቱ ሌላ በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ ከፍ ያለ ዋጋ እንዳለው የታወቀ ስለሆነ ፤ ለእንደዚህ ያለው በጎ ሥራ መሽቀዳደም አለብን ።

# እምነትና

## ፍ ቅ ር ።

እምነትና ፍቅር ተባብረው ቢሠሩ
ለዓለም ቤዛ የሚሆን ሰላምን ፈጠሩ ።

እርሱ ለእኛ ሲያስብ እኛ ለራሳችን
የእግዚአብሔርን ፍቅር አደረሰ ልባችን ።

በኢየሱስ ክርስቶስ የሆነው ስጦታ
እስከ ዘለዓለም የለውም ወረታ ።

የአዳም ልጅ በሙሉ ሞትን የተመኘ
እሥር የሚአስፈታ አንድ ሰው አገኘ ።

የማቴዎስ ወ. ም. ፯ ቁ. ፲፫ ይህ
ጠባቡ መንገድ የፍኖተ ጽድቅ
ከምዕራብ እንሥቶ ያደርሳል ምሥራቅ ።
በሰፊው ጐዳና ሕዝባችን እመራ
እንዲያው በእሽቅድድም ከቀኝ ወደግራ ።

በሰፊው ጎዳና በሰፊው መንገድ
ወንበዴው ብዙ ነው የትም አያስኬድ ።

ባያውቀው ይሆናል መንገዱን መርምሮ
ከታላቁ መምህር ትምህርቱን ተምሮ ።

እንዲጠነቀቁ በአንድ እምነት ያመኑ
ሕጉን እየጣሱ እንዳይኰነኑ
አስተምሮአቸዋል ጌታ በሥልጣኑ ።

ከሾህ የወይን ፍሬ ከበለስ ሽንኩርት
የሚለቅም ማነው ያልዘራውን ጥንት ።

እንዲሁ መልካም ዛፍ መልካሙን ያፈራል
ክፉም ዛፍ ከፍሬው ቀድሞ ያስታውቃል።

መልካም ዛፍ ከጥንቱ ክፉ ፍሬ ማፍራት
ክፉም ዛፍ ደግ ፍሬ እንደ ማይቻላት ።

ለእኛም ነው ፍሬያችን መልካም ሥራ
መሥራት ።

ክፉ ይቈረጣል ወደ እሳት ይጣላል ፤
መልካም ፍሬ ያለው ከቦታው ይኖራል ።

የነፃነት ጋሻ የተደላደለ
በኃይለ ሥላሴ አፍሪቃ ታደለ ።

የነፃነት ምርኩዝ ሁሉም ተመረኰዞ ፤
ተሻገረ ባሕሩን ተጉዞ ተጉዞ ።

የባሌ ጠ. ግዛት የወንጌል መልእክተኛ
ተወህበ ምህረት

# ስድስተኛ የወንጌል

## መልእክተኞች ጉዞ ።

የወንጌል መልእክተኞች ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ. ም. ከቀኑ በ፬ ሰዓት ጉዞ አቸውን ከአርማንያ ወደ ኤፍራታ ወረዳ ግ. ከራ ቆሬ ቀጥለው ሲጓዙ ሰንበቴ ከተማ ሲደርሱ እንደ አጋጣሚ አቶ ቡሱ በአንድ ምክንያት ሲቆም መልእክተኞቹ ወርደው በጐዳናው ሲመላለሱ አንድ ሠርግ ቤት አይተው ወደዚያው ጕራ አሉ ። በዳሱ ውስጥ ብዙ ሕዝብ ተሰብስበ በማየታቸው ከበሩ ላይ ቀረብ ብለው ገብቶ ለማስተማር ይቻላል ወይ? ብለው ፈቃድ ከባለቤቱ ጠየቁ።ባለቤቱም በደስታ በማን ዕድል ይኸማ ይሆንልኛ ብለው ፈቀዱ።የወንጌል መልእክተኞቹም ገብተው በቴፕ የተቀዳውን የቅዱስ ያሬድን ዜማ ሙሴኒ ርእያ የሚለውን የእመቤታችንን ክብር የሚገልጽ ዜማ ካሰሙ በኋላ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌል ማኅበር መላኪቸውን ገልጸው እኛ ሠርግ ቤት ገብተን የምናስ ተምረው ከሜዳ እንዳይመስላችሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት እናቱና ከተማሪዎቹ ጋር በቃና ዘገሊላ ማስተማሩንና ተአምራት ማድረጉን መሠረት በማድረግ ነው ብለው ገልጸዋል ። ሕዝቡ በደስታ ተውጦ እየተነሳ ሐሳቡን ሲገልጽ የዛሬይቱ ዕለት ሁለት ክብረ በዓል ያለባት ነች እሱም ሰንበትና የቅድስት ድንግል በዓል ሲሆን አሁንም የናንተ መምጣትና የሠርጉ ደስታ አርክቶናል ብለው ደስታቸውን ገልጸዋል ።

ከዚህ በኋላ ጉዞዋቸውን ቀጥለው ኤፍራታ ወረዳ ግዛት ከራ ቆሬ ከተማ በደረሱ ጊዜ የወረዳው ገዥ አቶ ክብረት ሻህ እርገጥና የወረዳው ዋና ጸሐፊ ፤ አቶ ሸዋ ቀና ባዩ የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ጓዶችም ከተናገሩ በኋላ የወረዳው ገዥ በቅንነት፣ በትጋት ባለሥልጣኖችንና የአገር ሽማግሌዎችን ካህናቱንም በጠቅላላ የከተማውን ሕዝብ ሰብስበው በግዛቱ ቅጥር ግቢ ተገኙ በዚህ ጊዜ መልእክተኞቹ ስለ ማኅበሩ ዓላማ በዝርዝር አሰምተዋል፤ ማኅበሩ ሕዝቡም ተደስቶ ወዲያውኑ ስለማኅበሩ ከዋና ፕሬዚዳንት እስከ አባሎች ድረስ መርጠ ማኅበሩን አቋቁመውዋል ፤ ስለተዋህዶ ሃይማኖትና የቤተ ክርስቲያናችን ባሕልን፣ሥርዓትን የሚያስረዱን ሰባኪዎች ከአውራጃው አንዳንድ ጊዜ እንዲላኩልን ብለው አሳስበዋል ።

## ፍቅር ከየት አለሽ ።

እስቲ በስመ አብ ብየ ልጀምር መገዘሙር፣
ፍቅር ያለሽበት ሰማይ ነው ወይ ምድር ?
ግብርሽ የረቀቀ ከሰዉ ሕሊና ፤
አድራሻሽ አይታወቅ ፈጽሞ ደመና ።
ዛሬ ታይተሽ እንደሁ ነገ ትጠፊያለሽ ፤
የዓለምን ሞራል ታሻግሪው አለሽ ።
ሁሉም ርስ በርሱ የሚተራመሰው ፤
ፍቅርን ስለአጣ ነው እየ ሰው ! እየ ሰው!
ጌታ በወንጌሉ ተናግሮ ነበር ፤
ወንድሙን እንዲወድ በጸና ፍቅር ።
በሕጉ መሠረት መከተል ሲገባ ፤
እዬ የኛ ነገር ሆነ ከንቱ አበባ ።
በል እስቲ ወዳጄ የት አይቼህ ነበር ፤
የገዛ አከላቱን ይጠይቀው ጀመር ።
እናትና ልጅም ሆነው በገበታ ፤
ምግቡ ሳይነሣ ይበዛል ዋካታ ።
እባክሽን ፍቅር በደህና አስታርቂያቸው፤
አንቺ ስትገቢ በጣሙን ሰላም ነው ።
ሐዋርያው ጳውሎስ ተናግሮ ነበር ፤
ዓለምን በፍቅር ለማስተሣሠር ።
ምንም ብመራመር እውቀቴ ቢልቅ ፤
በመላእክትም ቋንቋ መናገርም ባውቅ ፤
መፋቀር ከሌለኝ አይገኝም ጽድቅ ።

ከቅድስት ሥላሴ መ. ት. ቤት
ዮሐንስ ግላዝጊ

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ።

www.ethiopianorthodox.org